የሰ/መ/ቁ. 25567

ኀዳር 12 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሂም አህመድ

**አመልካች፡-** ወ/ት አይናለም አበበ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ ደገፋ ጉርሙ - ጠበቃ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በአመልካች ሰኔ 16 ቀን 1998 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በቀረበ ክርክር ሲሆን ፍሬ ነገሩም ያሁኑ ተጠሪ የሥር ከሣሽ በመሆን በሥር 1ኛ በመቃወም በተጠሪ ወ/ሮ ደስታ ይመር /በዚህ መዝገብ የሌሉበት/ እና ባሁኗ አመልካች የሥር 2ኛ በመቃወም ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ሟች ወንድማቸው አቶ አበበ ጉርሙ ልጅ አለመውለዱ እየታወቀ አመልካች የሟች ልጅ ናት ተብሎ ወራሽነቱ የተረጋገጠው ባግባቡ ስላልሆነ ውሣኔው ይሻር የሚል ነው፡፡ ለክሱም 1ኛ የመቃወም ተጠሪ በርግጥ አመልካች ከኔም ሆነ ከሟች አትወለድም ልጁ ነች ብዬ ውሣኔ ያሰጠሁት ከሕፃንነቷ ጀምሮ ስላሳደኳትና እንደ ልጅ ስለምቆጥራት ነው ሲሉ አመልካችም በበኩሏ ተጠሪ ሕፃን ሆኜ ውሣኔ ሲሰጥ ቀርበው መቃወም ሲችሉ ከ21 ዓመት በኋላ መቅረባቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1000 መሠረት ተቀባይነት የለውም በማለት በየበኩላቸው መልስ ሰጥተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000 የሚሠራው የፈረሰ ንብረት ይገባኛል ለሚል ክርክር እንጂ ወራሽ ናት አይደለችም ለሚል ክርክር አይደለም በሚል የይርጋ መቃወሚያውን ውድቅ አድርጎ አመልካች ከሟች የማትወለድ በመሆኑ ስለ ኑዛዜ ወራሽ ልትሆን አትችልም በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛው ፍርድ ቤትም በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ሟችና 1ኛ የመቃወም ተጠሪ በቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 143/ሠ/ መሠረት አመልካችን ወደ ቤት በመውሰድ፣ በማንከባከብና በማስተማር እንደ አባት በመሆን የተሣተፉ በመሆኑ አመልካች የሟች ልጅና የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ነች በማለት ወስኗል፡፡

ያሁኑ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር ተሰኝተው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍርድ ቤቱም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ሽሮ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች ይህን የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በዚህ መነሻነት ሲሆን ፍርድ ቤቱም አቤቱታውን መርምሮ ተጠሪን በማስቀረብ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡ ክርክሩንም ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በዚህም መሠረት አመልካች ኀዳር 5 ቀን 1993 ዓ.ም. የወራሽነት ማስረጃ ካገኙ በኋላ የሟች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆናቸውን በመግለጽ በቤቱ ላይ ያገኙት የጋራ ባለሀብትነት መብት /ከሥር 1ኛ የመቃወም ተጠሪ ጋር/ ተቀባይነት ያጣው ባግባቡ መሆን አለመሆኑን ፍርድ ቤቱ እንደሚከተለው ተመልክቷል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች ያቀረቡት ክርክር ባንድ በኩል የሟች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ነኝ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ከ20 ዓመት በላይ ቆይተው በቤቱ ላይ አለኝ የሚሉት የወራሽነት መብት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000 መሠረት የሚታገድ ነው የሚል ሲሆን የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የጠቀሱት የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000 ተፈፃሚነት ያለው የውርስ ንብረት ይገባኛልና ይሰጠኝ ለሚል ክርክር እንጂ ወራሽ ናት አይደለምችም ለሚል ክርክር አይደለም በማለት የሰጠውን ውሣኔ እንደተመለከትነው ድንጋጌው ባግባቡ አለመፈጸሙን ተረድተናል፡፡ ያሁኑ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ በራሱም ሲታይ ይዘቱ ወንድሜ ልጅ አለመውለዱ እየታወቀ አመልካች በሐሰት ልጅ ነኝ ብላ የወራሽነት ማስረጃ

የወሰደች ስለሆነ ትመልስ እንዲሁም በቤቱ ላይ ያለው የሟች ድርሻ ለኔ ይሰጠኝ የሚል ሲሆን አመልካችም በበኩሏ የሟች ልጅ መሆኗን እና ንብረቱም እንደሚገባት መከራከራቸው ከክርክሩ ትክክለኛ ገጽ ታይቷል፡፡ /ከክርክሩ ትክክለኛ ገጽ/ ይህ ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ክሱን ያመኑ ይመስል ገና ከጅምሩ ድንጋጌውን አጥብቦ በመተርጎም የልጅነት ጥያቄ ቢነሣ ድንጋጌው ተፈፃሚነት የለውም ማለቱ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ይህ ድንጋጌ መገኛው አንቀጽ 999 ሆኖ እውነተኛ ወራሽ እኔ ነኝ ከሚል ጥያቄ ጀምሮ የውርስ ንብረት ያላግባብ ተወስዷልና ይመለስልኝ በማለት የሚቀርቡትን ክሶች /ጥያቄዎች/ የሚያካትት ለመሆኑ አንቀጽ 999ን መመልከቱ ይበቃል፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች ክርክሩን ባስነሳው ቤት ላይ ከ20 ዓመት በላይ የቆየ የባለሀብትነት ድርሻ ማግኘታቸው እየተመለከትም፤ ተጠሪም ድርሻቸውን ለመጠየቅ ከሚያስችላቸው ጊዜ በላይ ቆይተው ክስ ለማቅረባቸው አመልካች ያቀረቡት የይርጋ ክርክር ተቀባይነት ያጣው ድንጋጌው በጠባቡ በሥር ፍርድ ቤት በመተረጎሙ ሳቢያ መሆኑን ይህ ፍ/ቤት ተገንዝቧል፡፡ በመሆኑም የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠው ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይርጋውን ነጥብ አልፎ ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት ምንም እንኳ የአመልካችን ልጅነት ተቀብሎ የሥር ፍ/ቤቱ ውሣኔ የሻረ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ለይርጋው ጥያቄ በቅድሚያ ምላሽ ቢሰጥ ኖሮ ወደዚህ ነጥብ መግባት የሚያስፈለገው እንዳልነበር ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ክሱ በይርጋ ታግዷል ብለናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 21679 ግንቦት 23 ቀን 1988 ዓ.ም. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 03562 ጥር 19 ቀን 1996 ዓ.ም. የሰጧቸው ውሣኔዎች ተሽረዋል፤ ይፃፍ፡፡
- የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 28193 ሐምሌ 27 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፤ ይፃፍ፡፡



- የከፍተኛ ፍርድ ቤት መ/ቁ. 28193 በመጣበት አኳኋን በመሸኛ ተመልሶ ይላክ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፡፡
- ክሱ በይርጋ ይታገዳል ተብሏል፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ